# የጨረታ ማስታወቂያ

ኢትዮ ቴሌኮም  የተለያዩ ያገለገሉ የከባድና ቀላል መኪኖች መለዋወጫዎችን ባሉበት ሁኔታ ለሕጋዊ ድርጅቶች በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ጨረታው የሚቆይበት ጊዜ ከመስከረም 18 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ 11:30 ሰዓት ድረስ፡፡

1/ ስለ አሻሻጡ ዝርዝር መግለጫ የያዘውን የጨረታ ሰነድ ከመስከረም 18 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ 10:00 ሰዓት ድረስ ከዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 214 የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይቻላል፡፡

2/ ያገለገሉ የከባድና ቀላል መኪና መለዋወጫዎችን ለማየት ለሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የገዙበትን ደረሰኝና መታወቂያ በመያዝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ (በቅሎ ቤት) አካባቢ በሚገኘው የኢትዮ ቴሌኮም ጋራጅ በመገኘት ከመስከረም 18 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 7 ቀን 2010 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 10:00 ሰዓት ድረስ መመልከት ይቻላል፡፡

3/ ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ውጤቱ እንደታወቀ የሚመለስ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ያገለገሉ የከባድና ቀላል መኪና መለዋወጫዎችን ለመግዛት የሚያቀርቡትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ( አምስት (ከመቶ) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡የጨረታ ማስከበሪያው ከታወቀ ባንክ ተረጋግጦ በሚቀርብ ሲፒኦ (CPO) ወይም በጥሬ ገንዘብ መሆን ይኖርበታል፡፡

4/ ተጫራቾች ያገለገሉ የከባድና ቀላል መኪና መለዋወጫዎችን የሚገዙበትን ዋጋ በተዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ/ፎርም መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በጥቅል ዋጋ ማቅረብ ከጨረታ ያሰርዛል፡፡ ተጫራቾች መግዛት የሚፈልጉትን ያገለገሉ የመኪና መለዋወጫዎችን የሚያሳይ የዋጋ ማስገቢያ ቅጽ/ፎርም፡ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ኮፒ፡ የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ (CPO) ፡ እንዲሁም የተጫራቾች አድራሻ መግለጫን በማካተት በታሸገ ኤንቨሎፕ ሙሉ አድራሻውንና የጨረታውን ቁጥር በመጥቀስ በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 214 ከመስከረም 18 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 7 ቀን 2010 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ 11:30 ሰዓት ድረስ ማስገባት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ከዚህ ቀንና ሰዓት በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም::

5/ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዋናው መ/ቤት ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 213 ጥቅምት 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ይከፈታል::

**ኢትዮ ቴሌኮም**